# የዘረኛና አምባገን አገዛዝ መሪን ለመቃወም ባንድነት እንነሳ

“Council of Ethiopian Communities in Canada” የሚባል ድርጅት ከትግራይ ድርጅት ጋር በመሆን ለዲክታር መለስ ዜናዊ ክብር ቅዳሜ ጁን 26 ምሽት በሃንጋሪያን ካናዲያን የባሕል ማዕከል የዕራት ግብዣ እንደሚያደርግ ወሬው እየተናፈሰ ነው።

በካናዳ የምንገኝ ኢትዮጵያውን ጠንቅቀን እንድምናውቀው በመለስ ዜናዊ የስለላ ድርጅት ሰልጥነው በኮሚኒቲአችን ውስጥ ወሬ እንዲለቃቅሙ የተላኩ ግለሰቦችና የመለሰ ደጋፊዎች የሆኑ የህወሃት ካድሬዎች የተሰባሰቡበት “የትግራይ ማህበር” ድርጅት ከመኖሩ በቀር “Council of Ethiopian Communities in Canada” የሚባል ድርጅት የለም።

በካናዳ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚወዱትና ሞቅ ያለ አቀባበል ያደረጉለት ለማስመሰል የመለስ ድጋፊዎች የሌለ ድርጅት በሃሳባቸው ፈጥረው ደፋ ቀና በማለት ላይ ይገኛሉ። የተቀባዩም ብዛት እንዲጨምር የአገዛዙ ጥቅመኞች ከየቦታው እንደሚሰባሰቡ ይጠበቃል።

በቶሮንቶ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ይህንን የዘረኝነት ቁንጮና ፋሽስት ግለ ሰብ በከተማችን መገኘት በመቃወም ታላቅና ታሪካዊ ሰልፍ እያዘጋጀን እንገኛለን። June 26-27 የሚደረገው ሰልፍ እንደተጠበቀ ሆኖ በሃንጋሪያን ካናዲያን የባህል ማእከል መለስ እራት መጋበዙ ከተረጋገጠ የወገኖቻችን በግፈኛ አገዛዝ ሥር መውደቁ የሚቆጨን ኢትዮጵያውን ሁሉ በነቂስ ወጥተን ተቃውሞአችንን እንድናሳይ ይዘጋጁ። በዚያውም በከተማችን የሚኖሩ አገራችንን በመሸጥ ላይ ያለውን የአገዛዝ ሥርዓት ደጋፊዎች እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ትልቅ አጋጣሚ ይፈጥርልናል።

የመለስ ደጋፊዎች ሰልፍ መዘጋጀቱ ስለማያስደስታቸው ቦታውን ሊቀይሩ ስለሚችሉ ትክክለኛውን መረጃ እንድንከታተል እያሳሰብን ያገኘነውን መረጃ በዚህ ድረ ገጽ ስለምናስታውቅ እንድትከታተሉ እናስታውቃለን።